# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፤ ቁጥር ፬ ፤ ነሐሴ ፳፻፲፫ ዓ.ም

**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት፡፡



**ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ለመላው ኢትዮጵያውያን 6.7 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል የተከላው ወቅት በስኬት ስለተጠናቀቀ የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክት አስተላልፈዋል**

## በዚህ እትም. . .


| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ የNAMA ኮምፖስት ፕሮጀክት | ፪ |
| ዜናዎች | ፪ |
| ሁነቶች | ፫ |
| 26ኛው ዓለማቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤና ኢትዮጵያ ቅድሚያ የምትሠጣቸው ጉዳዮች | ፯ |
| ልዩ ልዩ ሀትመቶች | ፯ |




**ዋና አዘጋጅ፡** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፡** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፡** መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡** አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፬

## ዜናዎች

### በኢትዮጵያ ቆላማ ሥርዐተ-ምህዳሮች የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮጀክት

የአለም አካባቢ ፋስልቲ በተሰኘ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሀገራት በሚመደብ ሀብት በኢትዮጵያ ውስጥ በተመረጡ ስድስት ክልሎች ውስጥ ባሉ አስራ ሁለት ወረዳዎች ለሚቀጥሉት ስድስት ዓመታት (እ.አ.አ. 2021-2027) የሚተገበር ፕሮጀክት ይፋ ተደርጓል።

ፕሮጀክቱ በወረዳዎቹ ለሚገኙ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ማህበረሰቦች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ይጠበቃል። ዓላማውም ዋና ዋና የሆኑ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ስልቶችን ግንዛቤ መጨመር ሲሆን፣ ይህም የማህበረሰብ-ተኮር የማጣጣሚያ ቴክኒኮች፣ በቀጣይ ለሚከሰቱ ስጋቶች ምላሽ የመስጠት ችሎታን ማሳደግ፣ የተራቆቱ ተፋሰሶች እንዲያገግሙ በሚሰሩ ስራዎች ተጠቃሚዎችን የመፍጠር፣ የማሻሻል እና የማስቀጠል እንዲሁም የመሬት አጠቃቀም አያያዝ ስርዐት አቅምን ማጠናከር ይጨምራል። ምንጭ

### የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን ተሳትፎ በ2021 በተካሄዱ የሚኒስትሮችና የልዑካን ስብሰባዎች

በለንደን እ.አ.አ. ከሀምሌ 24-26/2021 በተካሄዱ የሚኒስትሮችና የልዑካን ስብሰባዎች የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን በክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽነር መሪነት ተካፍሏል።

ስብሰባው የሀገራት የአካባቢ ሚኒስትሮች በቀጣይ በሚካሄደው የግላስጎው 26ኛው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ስለሚጠብቋቸው ውጤቶች ለመምከርና በአበይት ጉዳዮች ላይ የጋራ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው። የተነሱ ጉዳዮችም በፓሪሱ ስምምነት መግባባት የተደረሰበትን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ወደ 1.5 ማውረድ አቋም ማስቀጠል፣ የማጣጣሚያ እርምጃዎችን ድርሻ ማሳደግ፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥ የሆኑ ኪሳራዎችና ጉዳቶችን፣ የካርቦን ሽያጭን የሚመለከተው የአንቀጽ 6 እና በፋይናንስ ዙሪያ ላይ ያጠነጠኑ ነበሩ።

ልዑካኑ የመሪዎች ስብሰባው ላይ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሀገራት ቡድን ስም በግላስጎው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሀሳቦች አቅርቧል። ከቀረቡት ሀሳቦች መካከልም የሚኒስትሮች ስብሰባ ውጤትን በተለይም ሀገራት የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ቁርጠኝነታቸውን እንዲጨምሩ የሚለው ሀሳብ ታሳቢ የማድረግ አስፈላጊነት፣ የበለፀጉት ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥን ተፅኖ ለመቋቋም የገቡትን የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ስምምነታቸውን ለመፈፀም ቁርጠኝነታቸውን እንዲያሳዩ፣ አንዳንድ ቴክኒካዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ከጉባኤው ቀደም ብሎ የፖለቲካ ይሁንታን በሚሹ ጉዳዮች ላይ የጋራ ውይይት እንዲካሄድ የሚሉት ጉዳዮች አፅንኦት ተሰጥቶባቸዋል።

### የኢትዮጵያ የNAMA ኮምፖስት ፕሮጀክት

- ትዕግስት አለሙ፣ የከተማ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣም ቢሮ ኋላፊና የፕሮጀክት ዳይሬክተር እና አቶ ግርማ ወርቁ፣ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የፕሮጀክት አስተዳዳሪ

የኢትዮጵያ መንግስት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ (CRGE) ሰነድ ላይ በዝርዝር እንዳስቀመጠው እ.አ.አ. በ2025 ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ አልሟል። ከCRGE ስትራቴጂ በተጨማሪ ኢትዮጵያ የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝን እና የከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማትን የሚያቅፉና የከተማ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማትን የሚያግዙ በርካታ ስትራቴጂዎችን ነድፋለች።

በኢትዮጵያ የከተሞች መስፋፋት ከተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ እና ከከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማት አንፃር ከፍተኛ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን እያስከተለ ሲሆን ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- ከከተሞች የሚወጣው የደረቅ ቆሻሻ መጠን እየጨመረ መምጣት። ከከተሞች የሚወጣው ደረቅ ቆሻሻ የሚሰበሰበውና የሚጣለው በከፊል-የተገነቡ/የሳኒታሪ በታዎች ላይ ሲሆን ይህም የሜቴን-ጋዝ ልቀት እንዲጨምር አድርጓል።
- መደበኛ ባልሆኑ የሰፈራ በታዎች ላይ የህዝብ መጨመር ከመዘጋጃ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል። የዚህ ውጤት ቆሻሻ እንደ ክፍት በታዎችና የወንዝ ዳርቻዎች ያሉ ህዝብ የሚበዛባቸው ስፍራዎች ላይ እንዲጣል ሲያደርግ ከዚህም በተጨማሪ የከተማ አረንጓዴ በታዎችና የወንዝ ዳርቻዎች እንዲበላሹ አድርጓል።
- ታዳሽ-ሀይል ካልሆኑ የባዮማስ ምንጮች ከሚገኝ የሀይል ፍላጎት በከተሞች አካባቢ መጨመርና ከዚህም በተጨማሪ ለኮንስትራክሽን የሚያስፈልጉ የጣውላ ምርቶች ፍላጎት መጨመር የደን ምንጣሮንና መመናመን አስከትሏል።

ወደ ገፅ ፫

**ከገፅ ፪ የቀጠለ**

በ2009 ዓ.ም ይፋ የሆነው የኢትዮጵያ የNAMA ኮምፖስት (ማዘጋጃ ቤቶች የደረቅ ቆሻሻ ትራንስፎርሜሽንን የሚተገብሩበት ዕድል መፍጠር) ፕሮጀክት የተቀረፀው ሀገራዊ የዕድገት አላማን ለማሳካት የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝን እና የከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማት ዘዴዎችን ከተሞች እንዲጠቀሙ ለማበረታት ነው፡፡

ፕሮጀክቱ የሚከተሉትን ዓላማዎች ለማሳካት አቅዷል፤

- የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝን እና የከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማትን በከተማ ስርዐት ውስጥ ለማስረፅ የህግ ማዕቀፍንና የተቋማትን ቅንጅትን ማጠናከር፡፡
- የኮምፖስት ምርት አጠቃቀምንና የፋይናንስ ምንጭ ዘላቂነት ለማረጋገጥ የማይክሮና አነስተኛ ድርጅቶች በባለሙያ የሚደገፉበትን ገበያ-ተኮር ስርዐት መፍጠር፡፡
- ከፍተኛ የልቀት ቅነሳን ለማሳካት የተቀናጀ የከተማ ስርዐት አቅምን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያጎለግብት፤ ሀገራዊ ምቹ የማስተሰረያ የድርጊት መርሀ-ግብር (NAMA)ን መተግበር፡፡
- የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝን እና የከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማትን ማስተሳሰር የሚችል፤እንዲሁም በአግባቡ የሚለካን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳን ያካተተ የከተማ ስርዐትን በNAMA ማዕቀፍና ስር መተግበር፡፡

የኮምፖስት ፕሮጀክት በትግበራው መጨረሻ ምዕራፍ ከከተማ የአረንጓዴ መሰረተ-ልማትና የተቀናጀ የቆሻሻ አያያዝ ተግባራት 306,000 እና 132,321 ቶን የካርቦን እኩሌታ በቅደም ተከተል የመቀነስ አላማ አለው፡፡ ይህ ቅነሳ የሚገኘው ፕሮጀክቱ በየአመቱ ለአምስት አመታት ከሚያከናውነው 45,489 ቶን ከሚሆን ኮምፖስት፣ 151,629 ቶን ኦርጋኒክ ቆሻሻና 33,309 ሄክታር የተመናመነ መሬት ላይ በሚደረግ ተከላ ነው፡፡ ይህም ማለት የፕሮጀክቱ ትግበራ ጊዜን በ20 ዓመት ብናሰበው 8.33 ሚ/ሜ/ቶን የካርቦን እኩሌታ ቅነሳ ከፕሮጀክቱ ሊገኝ ይችላል፡፡ ከልቀት ቅነሳ በተጨማሪ ፕሮጀክቱ እንደ ስራ ዕድል ፈጠራ፣ በከተሞች አካባቢ ለአየር ንብረት ለውጥ አልበገሬነት፣ የአካባቢ ጥበቃና የኑሮ መሻሻል ያሉ በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡

ፕሮጀክቱ በስድስት ከተሞች ማለትም በአዳማ፣ በባህርዳር፣ በቢሾፍቱ፣ በድሬዳዋ፣ በሀዋሳና በመቀሌ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የፕሮጀክቱ ወጪ የሚሸፈነው በአለም-አቀፉ የአካባቢ ፋሲሊቲ እና በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ሲሆን በጥሬ ገንዘብና በአይነት ደግሞ ከተሞቹ እና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ድጋፍ አድርገዋል፡፡

**የፕሮጀክቱ ስኬቶች**

**የከተማ አረንጓዴ መሰረተ ልማት**

ተመሳሳይ ተግባራት ከሚያከናውኑ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት በመስራት ፕሮጀክቱ በስርዐት ዝርጋታ እንዲሁም በመሬት ላይ የሚታዩ አስደናቂ ስኬቶችን አስመዝግቧል፡፡ የፌዴራል የመሰረተ ልማት ዝርጋታና የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር የሚያወጣቸው ደንቦች ወደ ስድስት ከተሞች ተሰራጭተዋል፡፡ የማዘጋጃ ቤት ባለሙያዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንደ የከተማ የአካባቢ ጥበቃ፣ የከተማ መሬት አስተዳደርና የከተማ ግብርና ቢሮ ባለሙያዎች ስልጠና አግኝተዋል፡፡ ከተሞች የአረንጓዴ ሽፋን ተግባራትንና የቆሻሻ አያያዝ ተግባራትን ለማከናወን እንዲረዳቸው በአሁኑ ወቅት ደንቦቹን እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ፡፡

ፕሮጀክቱ በሶስት ከተሞች ላይ የችግኝ ማፍያ ጣቢያ እንዲቋቋም እያደረገ ሲሆን እነዚህም በመቀሌ 1,500,000 ችግኝ/በአመት፣ በድሬዳዋ 2,600,000 ችግኝ/አመት እና በባህርዳር 2,000,000 ችግኝ/በአመት የማፍላት ብቃት ያላቸው ጣቢያዎች ናቸው፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ የቢሾፍቱና የአዳማ ችግኝ ጣቢያዎች የማፍላት ችሎታ በ800% (2.2 ሚሊዮን/በዓመት) እና በ600% (2.5 ሚሊዮን/በዓመት) በቅደም ተከተል እንዲጨምር አድርጓል፡፡ ችግኝ ማፍላት ላይ ዝርያ በመምረጥ ረገድ መመሪያ በመስጠት ፕሮጀክቱ ለእያንዳንዱ ከተማ አግሮ-ኢኮሎጂ ሁኔታ ምቹ የሆነ የዛፍ ዝርያ የለየ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የውሀ ማጠራቀሚያዎችንም አቅርቧል፡፡

ወደ ገፅ ፬

**ከገፅ ፫ የቀጠለ**

ከዚህ ቀደም ቢሸፍቱ ከተማ በሀገሪቱ የችግኝ ብቸኛ ምንጭ የነበረች ሲሆን ሌሎች ከተሞችም ችግኝ ለመግዛት ረጅም መንገድ መጓዝ ይጠበቅባቸው ነበር። ይህም አንድ ዛፍ ለመትከል የሚያስፈልገውን ወጪ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል። በዚህ ፕሮጀክት ድጋፍ ተጨማሪ አምስት ከተሞች ለራሳቸውና ለአጎራባች ከተሞች የችግኝ ምንጭ ሆነዋል። አነስተኛና መለስተኛ ድርጅቶች ወደ ችግኝ ማፍላት ንግድ እንዲገቡ ስልጠናና በጣቢያው ለሚቀጠሩት ደግሞ የምስክር ወረቀት በመስጠት ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።ከደን ልማት ፕሮግራሞች ጋር የገበያ ትስስር መፍጠሩ ተጨማሪ የገበያ አማራጮች እስኪገኝ ድረስ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ አስችሏቸዋል።

በተደጋጋሚ ጊዜ በሚሰጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችና ችግኞች በነፃ በመቅረባቸው ምክንያት በስድስቱ ከተሞች የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በጓሯቸውና በአካባቢያቸው ዛፎችን እየተከሉ ይገኛሉ። ከዚህም በተጨማሪ በዛፍ ተከላ ወቅት የማህበረሰብ ተሳትፎ ጨምሯል፣ የቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች ታድሰዋል፣ የተጎዱ ቦታዎች እንዲያገግሙ ተደርጓል፤ በከተሞች ዳርቻ ያሉ አካባቢዎችም በደን ተሸፍነዋል። በዚህም የተነሳ የከተሞች የደን ሽፋን ጨምሯል።

ከተማን በአረንጓዴ በመሸፈን የሚሳተፉ ማህበረሰቦች፣ በደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ንግድ የተሰማሩ እና በመንግስት የችግኝ ማፍያ ጣቢያና በቆሻሻ አስተዳደር ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ባለሙያዎች ስልጠና በአግባቡ ያገኙና የብቃት ማረጋገጫ የግምገማ ሂደትን ካለፉ በኋላ ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 3 የምስክር ወረቀት አግኝተዋል። ይህም ከተሞችን በአረንጓዴ በመሸፈን ትግበራ ያለውን የክህሎትና የእውቀት ክፍተት ያጠበበ ሲሆን ዘርፉም ውጤታማ እንዲሆን አስችሏል። በዚህም ምክንያት መካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶች ከተሞችን በአረንጓዴ በማልበስና ተያያዥ ስራዎች እንዲሳተፉ ያደረገ ሲሆን፣ የፈላ ችግኝ ቁጥር ሽያጭና በፓርኮች አስተዳደር ተሳትፎ ጨምሯል። በዚህ ዘርፍ 47,459 ለሚሆኑ ማህበረሰቦች ቋሚና ጊዜያዊ ስራዎች የተፈጠረ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 50 በመቶ ሴቶች ናቸው።

## የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር

ፕሮጀክቱ በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ዙሪያ ከሰራቸው መካከል በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና ልየታ ላይ የማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲጨምር ማድረግ ሲሆን ይህም የተከናወነው ቤት ለቤት በመሄድ፣ በትምህርት ቤቶች በሚደረግ ፕሮግራም፣ የማህበረሰብ ማነቃቂያ ፕሮግራሞች እንዲሁም እንደ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያሉ ሀገራዊና አካባቢያዊ የእትምና ከእትም ውጪ ያሉ የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ነው። ከዚህም በመቀጠል ቆሻሻዎችን ለመለየት እንዲያበረታታ ሞዴል መንደሮችን በመምረጥ የተለያየ ቀለም ያላቸው የቆሻሻ መጣያ ቀረጢቶች ተሰራጭተዋል። የመጀመሪያ ደረጃ ቆሻሻ የሚሰበስቡ መካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶችም ማህበረሰቡን እንዲያስተምሩና ቆሻሻን ከምንጩ በመለየት ስራ ላይ እንዲያሳትፉ ሀላፊነት ተሰጥቷቸዋል። በተመሳሳይም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ባለባቸው ቦታዎች ላይ የተለያዩ ቀለም የተደረገባቸው የቆሻሻ መጣያዎች ለእግረኞች እንዲቀመጡ ተደርጓል።

ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ ትግበራት ምክንያት በማህበረሰብ የባህሪ ለውጥ ተስተውሏል። በሞዴል መንደር የሚኖሩ ማህበረሰቦች ቆሻሻን ከምንጩ የመለየትና ከቤቶቻቸው የሚወጣውን ቆሻሻ በአግባቡ መጣል ጀምረዋል። ከበፊቱ የፕሮጀክት የትግበራ ዘመን ጋር ሲነፃፀር ሞዴል መንደሮች በመደበኛ ሁኔታ እየፀዱ ሲሆን ህጋዊ ያልሆኑ የቆሻሻ መጣያ ስፍራዎችም እየቀነሱ መጥቷል። አንዳንድ በግቢያቸው በቂ ቦታ ያላቸው ቤተሰቦች አነስተኛ ደረጃ ያለው የኮምፖስት ስራ በቤታቸው ውስጥ የጀመሩ ሲሆን ይህንንም የጓሮ አትክልቶቻቸውን ለማልማት ይጠቀሙበታል።

የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ትግበራ በስድስቱ ከተሞች ውስጥ የቆሻሻ አሰባሰብን ለማሻሻልና ለማጓጓዝ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ለመዘጋጃ አመራሩና ባልደረቦች በደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ዙሪያ በርካታ ስልጠናዎች የተሰጡ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ውስብስብ የቆሻሻ አስተዳደር ስርዐት ያላቸው ሃገሮች ጋር በመሄድም የልምድ ልውውጥ ተደርጓል። በቆሻሻ ስብሰባና ትራንስፖርት ላይ ለሚሳተፉ ስልጠናና የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ እየተደረገ ሲሆን ይህም በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ትግበራ እንዲኖር አስችሏል።

**ወደ ገፅ ፭**

## ሁነቶች

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- የከተሞች የሽግግር ጉባኤ፣ ክላይሜት አክሽን፣ መስከረም 2021 | **ምንጭ**
- 2021 የአየር ንብረት የሥራ ጉባኤ፣ ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ፣ መስከረም 2021 | **ምንጭ**
- 2ኛው አየር ንብረት ፍትህ ዓለማቀፍ መድረክ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ፍትህ መድረክ፣ መስከረም 2021 | **ምንጭ**
- "ትሮፐንታግ" 2021 - በግብርና ዘርፍ የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ጤንነትና እና ዘላቂነትን ማረጋገጥ፣ ሲፎር፣ መስከረም 2021 | **ምንጭ**
- ስርዐተ ፆታን የአየር ንብረት ለውጥ ደህንነት ማዕከል ማድረግ፣ ሲጂአይኤአር፣ ጥቅምት 2021 | **ምንጭ**
- በአጽኦት ማሰብ ተከታታይ ፕሮግራም፣ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ጥቅምት 2021 | **ምንጭ**
- የሃይድሮጂን ሽግግር ጉባኤ፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | **ምንጭ**
- የዘላቂ ፈጠራ መድረክ 2021፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | **ምንጭ**
- በአፍሪካ ውስጥ ዘላቂ የእንጨት ማገዶ እሴት ሰንሰለቶች አስተዳደር፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ምዳራዊ ልኬቶች፣ ሲፎር፣ ህዳር 2021 | **ምንጭ**

**ከገፅ ፬ የቀጠለ**

ፕሮጀክቱ በተጨማሪም በሙያ ጤናና የደህንነት ሂደቶች ዙሪያ ስልጠና የሰጠ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ለተሰማሩ ደግሞ የደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶችን አሰራጭቷል። በፕሮጀክቱ ድጋፍ በቡና ማፍላት እና ችግኝ በማፍላት ተግባር የተሰማሩ የመካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶችን በመጠቀም ማዘጋጃዎች ህጋዊ ያልሆኑ የቆሻሻ መጣያ ስፈራዎችን እንዲያፀዱ፣ የወንዝ ዳርቻዎችን ወደ ችግኝ ማፍያ ቦታዎችና መዝናኛ ቦታዎች እንዲቀየሩ ተደርጓል።

በስድስቱ ከተሞች የኮምፖስት ጅማሮና መስፋፋት የከተሞቹ የቆሻሻ አሰባሰብና አጓጓዝ ሂደቶች እንዲሻሻሉ አስተዋጽኦ አድርጓል።ፕሮጀክቱ 18,900 ሜትር ስኩዬር ስፋትና በአመት 86,000 ቶን የማምረት ችሎታ ያላቸው ስድስት የኮምፖስት ቦታዎች እንዲዘጋጁ ድጋፍ አድርጓል። በታዎቹን ከመገንባት በተጨማሪ ፕሮጀክቱ የኮምፖስት ደንብ እና ማኑዋል እንዲዘጋጅ ድጋፍ ያደረገ ሲሆን ለመካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶች በኮምፖስት ዝግጅት ዙሪያ ስልጠና እንዲያገኙ ረድቷል። ከዚህም በተጨማሪ መሰረታዊ ቁሳቁሶችን እንደ የኮምፖስት መሸፈኛ፣ የሙቀት መለኪያ እና በከፊል አውቶማቲክ የሆኑ የኮምፖስት ማሽኖችን የለገሰ ሲሆን ይህም የኮምፖስት ጥራትና ብዛት እንዲያድግ አስችሏል። እስካሁን ድረስ 210,460 ቶን ከሚሆን ቆሻሻ 68,830 ቶን ኮምፖስት ተዘጋጅቷል።

የኮምፖስቱ የካርቦን እና ሃይድሮጅን ይዘት፣ የ PH እና የእርጥበት መጠን በናሙናዎች ላይ በላቦራቶሪ የተካሄደ ሲሆን ጥቃቅን እና አነስተኛ ድርጅቶችም በአቅራቢያቸው ካሉ የግብርና ምርምር ተቋማት እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ለወድፊቱ ጥሩ ግንኙነት ፈጥረዋል። የኮምፖስቱ ዋና ተጠቃሚዎች፣የከተማው አስተዳደር (ለችግኝ ጣቢያ እና ለከተማ የተከላ እንቅስቃሴዎች)፣ የከተማ የሴፍቲኔት ፕሮግራም (ለከተማ ተከላዎች)፣ የንግድ ድርጅቶች (ለግቢያቸው) እንዲሁም ግለሰቦች (ለቤታቸው የአትክልት ቦታ) ናቸው።

ፕሮጀክቱ በስድስት ከተሞች ላይ ደረቅ ቆሻሻ እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል ትግበራ እንዲጀመርና እንዲጠናከር አስተዋፅኦ አድርጓል። መካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶች እንደ ወረቀት፣ ፕላስቲክ ጠርሙስና ብረታ-ብረት ያሉ እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉ ቁሳቁሶችን እንዲሰበስቡና እንዲሸጡ የማደራጀትና የመደገፍ ስራ የተከናወነ ሲሆን በዚህም ረገድ እስካሁን ድረስ 65,000 ቶን እንደገና መዋል የሚችል ቆሻሻ የመሰብሰብ ስራ ተከናውኗል።

በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ተግባራት እንዲሻሻሉ ከማድረግ በተጨማሪ የስራ ዕድል ፈጠራ ጠቀሜታ አላቸው። በዚህም ረገድ እስካሁን ድረስ 20,592 ለሚሆኑ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ ስራ የተፈጠረ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 50% ሴቶች ናቸው።

**ወደ ገፅ ፮**

ከገፅ ፭ የቀጠለ

## ከፕሮጀክቱ የሚገኙ ጥቅሞች

ፕሮጀክቱ ከላይ የተዘረዘሩትን በርካታ ጠቀሜታዎች ለማስገኘት በሚረዳ መልኩ ተቀርፅዋል፡፡ በፕሮጀክቱ 4 የትግበራ አመታት ፕሮጀክቱ በስድስቱ የፕሮጀክት ቦታዎች አካባቢያዊና ማህበረሰባዊ ጥቅሞች ያስገኘ ሲሆን እነዚህም፤

### አካባቢያዊ ጥቅሞች

በስድሰቱ ከተሞች በፕሮጀክቱ የቆሻሻ አስተዳደርና ከተሞች አረንጓዴ የማልበስ ተግባራት የመጡት ለውጦች ከዚህ ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች አዎንታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎች እንዲገኙ አስችሏል፡፡ እነዚህም፤

- ከቤት የሚወጡ ህገወጥ የቆሻሻ አወጋገዶች መቀነስ፡፡
- ለመዘጋጃዎች ቆሻሻን የመለየትና የማስተዳደር አዳጋች ሁኔታዎች መቀነስ፡፡
- የቆሻሻ አሰባሰብ ደረጃ መጨመር፡፡ ለምሳሌ የውሀ ጠርሙሶች የፍሳሽ ቦዮችን በመዝጋት በከተሞች ከፍተኛ ችግር ይፈጥሩ ነበር፡፡ ቆሻሻዎች እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ንግድ ከተጀመረ በኋላ ግን መካከለኛና አነስተኛ ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ቆሻሻን የሚሰበስቡ ግለሰቦች እነዚህን ጠርሙሶች ገንዘብ ለማግኘት መሰብሰብና መሸጥ በመጀመራቸው ችግሩ ተቀርፏል፡፡
- ኮምፖስትን በማምረትና ከተሞችን በአረንጓዴ በመሸፈን ከዘርፉ ከሚወጣው የሜቴን እና ካርቦን-ዳይኦክሳይድ ጋዞች ሊለቀቅ ይችል የነበር የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን መቀነስ፡፡ በዚህ ረገድ ፕሮጀክቱ ከኮምፖስትና ከተሞችን በአረንጓዴ ከመሸፈን 128,089 ቶን ካርቦን-ዳይኦክሳይድ እኩሌታ እንዲቀነስ አስችሏል፡፡
- ከተሞችን በአረንጓዴ ዕፅዋት ለመሸፈን በሚደረገው ጥረት ኬሚካል ማዳበሪያን ከመጠቀም ይልቅ ኮምፖስትን መጠቀም መጀመሩ፡፡
- የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራ በመከናወኑ፣ ዛፎች በመተከላቸውና በተከለሉ የማገገሚያ ስፍራዎች ምክንያት የእፅዋት ሽፋን በመጨመሩ የመሬት መሸርሸር የተወገደ ሲሆን የእፅዋት በተፈጥሮ የመብቀል ሁኔታም ጨምሯል፡፡
- የጉጦችና የተጎዱ ስፍራዎች እንዲያገግሙ በመደረጋቸው ምክንያት ሀይቆችና ወንዞች በደለል መሞላታቸው መቀነሱ፡፡
- ህብረተሰቡ በግቢው፣ በመንገድ ዳር፣ በፓርኮችና በአካባቢው ዛፎችን በመትከሉ ምክንያት የከፍተኛ ሙቀት መስተዋል መቀነሱ፤ ከዚህም በተጨማሪ የከተማው ህብረተሰብ ለአየር ንብረት ለውጥ አልበገሬነቱ ጨምሯል፡፡
- አዲስና ነባር ችግኝ ማፍያ ጣሚያዎች ችግኝ የማምረት ችሎታቸው መጨመሩ የአካባቢውና የመንግስት የዛፍ ተከላ ፕሮግራሞችን ያገዘ ሲሆን ለዛፍ ሽፋን መጨመርም አሰትዋፅዎ አድርጓል፡፡
- ማህበረሰቡን እና ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶችን የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴዎች እንዲያስተዳድሩ በማድረግ እና የባለቤትነት ስሜትን በመፍጠር የእንቅስቃሴዎቹን ዘላቂነት ማረጋገጥ፡፡

### ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች

- በአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች ምክንያት የጎርፍ መቀነስና የተክሎች ሽፋን መጨመር የከተማ መሰረተ ልማት እንዳይጎዳና ለጥገና ከመንግስትና ከማህበረሰቡ ሊወጣ ይችል የነበረውን ወጪ እንዲቀንስ አስችሏል፡፡ የአዳማ ከተማ ውበትና መናፈሻ ቢሮ የቡድን መሪ እንደገለፁት ‹‹ባለፈው ክረምት የነበረውን አይነት ዝናብ አይተን አናውቅም ነበር ሆኖም ግን ዝናቡ ይህ ነው እሚባል ጎርፍ አላስከተለም፡፡ ይህ ፕሮጀክት ከመተግበሩ በፊት ትንሽ መጠን ያለው ዝናብ ጎርፍ ለማስከተል በቂ ነበር፡፡›› ይህም ፕሮጀክቱ በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ ለሚከሰቱ እንደ ጎርፍና ከፍተኛ ሙቀት ያሉ ተፅዕኖዎችን የስድስቱ ከተማ ነዋሪዎች እንዲቋቋሙ ያደረገውን አስተዋፅኦ ማሳያ ነው፡፡
- ከህብረተሰቡ ጋር የተፈጠረው አጋርነት ህብረተሰቡ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣና አካባቢን በአረንጓዴ መሸፈን ያለውን ጠቀሜታ እንዲረዳ ያደረገ ሲሆን፤ ይህም በነዚህ ከተሞች በቀላሉ የሚስተዋል ለውጥ እንዲኖር አስችሏል፡፡
- አንዳንዶቹ እንዲያገግሙ የተደረጉ ቦታዎችና ለጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የተሰጡ የችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች፤ ህገ-ወጥ የቆሻሻ ቦታ መጣያ ስፍራ የነበሩ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሁለቱ የቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች የነበሩና ሰው ለማለፍ የሚጠየፉቸው ቦታዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ ስፍራዎች እንዲያገግሙ ከተደረጉ በኋላ ግን የጤና ጠንቅ መሆናቸው ቀርቶ ህብረተሰቡ ለምርቃትና ለሰርግ የሚጠቀምባቸው ቦታዎች ሆነዋል፡፡ በአቅራቢያ ያለ መሬት ዋጋና የቤት ኪራይም በዚህ ምክንያት ጨምሯል፡፡
- ፕሮጀክቱ ከከተማ ከሚወጣ ደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት የሚዘጋጅበትን ቴክኖሎጂ ያስገባ ሲሆን ባለፉት አራት አመታት ውስጥም ወደሁሉም ከተሞች የማስፋፋት ስራ አከናውኗል፡፡
- በእሴት ሰንሰለቱ ዙሪያ 68,051 ለሚሆኑ ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ ስራ ተፈጥሯል ፡፡ ስልጠናዎቹና የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞቹ ህብረተሰቡ ከተማን በአረንጓዴ በመሸፈንና በቆሻሻ አያያዝ ዙሪያ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጣ አስችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ ከተሞቹ አረንጓዴና ንፁህ ሁነዋል፡፡

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፤ ቁጥር ፬


## ልዩ ልዩ ህትመቶች

### የአየር ንብረት ለውጥ 2021፤ የቁሳዊ ሳይንስ መሠረት




በቅርቡ የወጣው የመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ፓናል የባለሞያዎች ቡድን አንድ ሪፖርት በሚቀጥሉት አሥርተ ዓመታት ውስጥ የዓለም ሙቀት መጠን ከ1.5 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የማለፍ እድል እንዳለው አዲስ ግምቶችን ይሰጣል። እንደ ሪፖርቱ ግምት ከሆነ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀቶች ላይ ፈጣንና መጠነ ሰፊ ቅነሳ ካልተደረገ የሙቀት መጠኑን በ 1.5 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ማስቆም ቀርቶ ወደ 2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ እንኳን ለመቅረብ ከአቅም በላይ ይሆናል። **ምንጭ**

### የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እርምጃዎች የኪስ መመሪያ




‹የምላሽ እርምጃዎች› የሚለው ሀረግ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአየር ንብረት ማዕቀፋዊ ስምምነት የስራ ሂደቶች ውጭ በመደበኛነት ጥቅም ላይ አይውልም። በዚህም የተነሳ የሀረጉ ትርጉም በስራው ሂደት ውስጥ ለሚገኙ ፖሊሲ አውጪዎች እና ባለድርሻ አካላት ዘንድ እንኳን ግልጽ አይደለም። ይህ መመሪያም በተመድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት አካላት በተለይም በተደራዳሪዎች ዘንድ ስለ ርዕሰ ጉዳዩን አስመልክቶ ግንዛቤ ለማሳደግ ያለመ ነው። **ምንጭ**

### ለዘላቂ የአየር ንብረት ለውጥ አገልግሎቶች መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፤ የአፍሪካ ተሞክሮ




ይህ ቴክኒካዊ ሪፖርት የአየር ንብረት እና የአየር ንብረት መረጃ አገልግሎቶች ለአፍሪካ የተባሉት ፕሮጀክቶች ውጤታማ የአየር ንብረት አገልግሎቶችን አቅርቦት ዘላቂ አቅም ፈጥረዋል ወይ በሚል የተከናወነውን ጥናት ግኝቶች ያቀርባል። **ምንጭ**

## 26ኛው ዓለማቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤና ኢትዮጵያ ቅድሚያ የምትሠጣቸው ጉዳዮች

❑ *በ አካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን*

**መግቢያ**

የፓሪስ ስምምነት ከተፀደቀ አምስት ዓመታት አልፈዋል። ይሁንና ስምምነቱን ወደተግባር ለመተርጎም የሚያስችለው የአፈፃፀም መመሪያ ሰነድ አልተጠናቀቀም። በርካታ የአየር ንብረት ለውጥ ሳይንቲስቶች፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና የአየር ንብረት ለውጥ ተሟጋቾች እ.አ.አ. 2021 በዓለም ዙሪያ የአየር ንብረት ለውጥን ተፅዕኖዎች ቅነሳ በተግባር ለመታገል ወሳኝ ዓመት መሆኑን ይስማማሉ። ይሁንና በኮቪድ ወረርሽኝ መከሰት ምክንያት ለአንድ ዓመት የተላለፈው 26ኛው የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ እ.አ.አ. ከጥቅምት 31 እስከ ህዳር 12 ቀን 2021 በሀገረ እንግሊዝ ፕሬዝዳንትነት በግላስጎ የሚካሄደው የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ እ.አ.አ 2020 በኋላ ለሚከናወኑ የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ተግባራዊነት ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው ይታመናል። ሆኖም የግላስጎውን 26ኛው የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ የተሳካ ለማድረግ አስቀድመው መፍታት የሚያስፈልጋቸው የተለያዩ አከራካሪ ጉዳዮች አሉ። ከነዚህም ጉዳዮች መካከል በ24 ኛውና በ25ኛው ጉባኤዎች መቋጫ ሳይበጅላቸው ተንከባለው የመጡ በስምምነቱ አንቀፅ 6 ላይ የሰፈረው "የካርቦን ግብይትን" የሚመለከተው ጉዳይና በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሀገራት በግልፀኝነት የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳቸውን ዘገባ የሚያቀርቡበት የጊዜ ገደብ ከመቼ ጀምሮ ይሁን? የሚሉ ያልተጠናቀቁ ርዕሶች ይገኙበታል።

በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው 26ኛው የተመድ አባል ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤን አስፈላጊነት ከግምት በማስገባት በቀጣዩ የግላስጎ የአየር ንብረት ለውጥ ድርድር ኢትዮጵያ ቅድሚያ ሰጥታ የምትደራደርባቸውን ቁልፍ ጉዳዮች አስፈላጊነት በማመን የአርታኢ ቡድናችን በዚህ "ኤን. ዲ. ሲ. ሀይላይት" በተሰኘ የኮሚሽኑ ዜና መፅሄት ላይ አንዳንድ ቁልፍ ጉዳዮች ሽፋን ለመስጠት ወስኗል። በዚህም ለረጅም ጊዜ ሲጠበቅ በነበረው 26ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ በጉባኤው ለማስመዝገብ ተስፋ የምታደርግባቸው እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለማብራራት ሙከራ ተደርጓል።

### በ26ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ትኩረት የሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

26ኛው ዓለማቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ የፓሪስ ስምምነትን በአጠቃላይ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ በ24ኛውና በ25ኛው ጉባኤዎች ተጀምረው መቋጫ ሳይበጅላቸው በይደር የቆዩ ነገር ግን ስምምነቱን ወደተግባር ለማስገባት አይነተኛ ሚና ያላቸው ጉዳዮችን ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚቋጫቸው ይጠበቃል።

**ወደ ገፅ ፰**

**ከገፅ ፯ የቀጠለ**

እነዚህ በ24ኛውና በ25ኛው ዓለምአቀፍ የአባል ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤዎች ድርድሮች መቋጫ ሳያገኙ ወደ 26ኛው የድርድር ጉባኤ የተሸጋገሩና የ26ኛውን ጉባኤ ስኬታማነት የሚወስኑ ቁልፍ ጉዳዮችም እንደሚከተለው በግልፅ ተጠቅሰዋል።

**የፓሪስ ስምምነት አንቀጽ 6ን አስመልክቶ በትብብር ስለመስራት:-** በ26ኛው የአባል ሀገራቱ የአየር ንብረት ለውጥ ድርድር ላይ መቋጫ መፍትሄ ከሚፈልጉ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ በፓሪስ ስምምነት አንቀጽ 6 ስር የሰፈረውና "የካርቦን ግብይት ዘዴዎችን" የሚመለከተው ጉዳይ ነው። ያለፉት ሁለት ጉባኤዎች በዚህ አጀንዳ ላይ ተጨባጭ ውጤቶችን ማቅረብ አለመቻላቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በግላስጎው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ላይ አጀንዳውን በተመለከተ የጋራ መግባባት ላይ ይደረሳል የሚል ከፍተኛ ተስፋ በተደራዳሪዎች ዘንድ አለ። ይሁንና አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታዎች ሲታዩ በተደራዳሪዎቹ መካከል በበርካታ ጉዳዮች ላይ ግልፅ የሆኑ ልዩነቶች ይስተዋላሉ። ከነዚህም የልዩነት ሀሳቦች መካከል በአጠቃላይ ዓለማቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳን እውን ለማድረግ መወሰድ በሚኖርባቸው የማስተሰርያ እርምጃዎችና ለተከናወኑ ስራዎች የሚመጥን ማካካሻን ለመተግበር የሚያስችሉ አሠራሮችን በተመለከተ፣ የማጣጣምያ ፈንድን የጥቅም ተጋሪነት አስመልክቶ ድርድሩ የካርበን ሽያጭን በሚመለከተው የፓሪሱ ስምምነት አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 6.2. ስር መከናወን ስለመቻሉ እና የድርሻው መጠንን አስመልክቶ፣ እና በኪዮቶ ፕሮቶኮል ስምምነት ተደርሶባቸው ሳይጠናቀቁ የተንከባለሉ ጉዳዮችን የተመለከቱ ናቸው።

**የተሻሻለ የግልጽነት ማዕቀፍን በተመለከተ:-** ምንም እንኳ የተሻሻለ የግልጽነት ማዕቀፍ ማስፈፀሚያ መመሪያ ሰነድ በ24ኛው ጉባኤ ተቀባይነት ያገኘ ቢሆንም በ26ኛው ጉባኤም ይጠናቀቃሉ ተብለው የሚጠበቁ ተጨማሪ የድርድር ግዴታዎች አሉ። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል በድርድር ሂደት ላይ ያሉ የሀገራት ዝርዝር የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዘገባዎች አቀራረብን አስመልክቶ፣ በየሁለት ዓመቱ የሚከናወን የቅነሳ ዘገባዎች ግልጽነትን አስመልክቶ፣ የቴክኒክ ባለሙያ ግምገማ ሪፖርቶችን አስመልክቶ፣ የተለመዱ የትርጓሜ ቅርፆችን አስመልክቶ፣ መዋቅራዊ ማጠቃለያ እንዲሁም የተለመዱ የሪፖርት ሰንጠረዦች ዝርዝር መግለጫዎችን በተመለከተ ቀጣይ ድርድሮችን ማካሄድ የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው። በመሆኑም ሀገራት እ.አ.አ. በ2024 የመጀመሪያውን በየሁለት አመቱ የሚቀርበውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳቸውን ዘገባ እንዲያቀርቡ ስለሚጠበቅ በዚህ አጀንዳ ስር ያሉ ጉዳዮች ላይ ድርድርን ማጠናቀቅ ወሳኝ ነው።

**የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ:-** 26ኛው ዓለማቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ትኩረት አድርጎ ከሚያያቸውና ከ25ኛው ጉባኤ ተንከባለው ከመጡ ጉዳዮች መካከል የአየር ንብረት ፋይናንስንም ይመለከታል። ይህ አጀንዳ በተለይ ከታዳጊ አገራት አንፃር ሲታይ በጣም ወሳኝ የሚያደርገው ያደጉ ሀገራት በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት እ.ኤ.አ. በ 2020 በየዓመቱ 100 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ የተገባው ቃል ገና ስላልተሟላ ነው። በ25ኛው የአየር ንብረት ጉባኤ ወቅት በዚህ ንጥል አጀንዳ ላይ የተደረጉት ድርድሮች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መግባባት ሳይቻል ቀርቷል። ከነዚህ መግባባት ካልተደረሰባቸው ጉዳዮች መካከልም የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ ትርጓሜ፣ ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ የገንዘብ ፍሰትን ለመገምገም የሚያስችሉ ዘዴዎች እንዲሁም ያደጉ አገራት ለታዳጊ ሀገራት እ.አ.አ. በ2020 100 ቢሊዮን ዶላር ለመስጠት የገቡትን ቃል ለመፈፀም ቁርጠኝነት ያለማሳየታቸው ስጋቶች ናቸው። በመሆኑም አባል ሀገራቱ ከአየር ንብረት ፋይናንስ ጋር በተያያዙ አንዳንድ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ ይደርሳሉ ተብሎ ይጠበቃል። ከሁሉም በላይ ግን በ26ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ላይ ሀገራት በአዲሱ የረጅም ጊዜ የአየር ንብረት ለውጥ የፋይናንስ ግብ ላይ ውሳኔ ላይ መድረስ ይኖርበታል።

**በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ላይ የጋራ የጊዜ ገደቦች መኖር:-**
በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ትግበራ የጋራ የጊዜ ማዕቀፍ አስፈላጊነት በፓሪስ ስምምነት መሠረት የተደነገገ ሲሆን በ24ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ላይ የጋራ የትግበራ የጊዜ ገደብ ስምምነት እንዲደረስም ታስቦ ድርድሮቹ ባለመሳካታቸው ድርድሮች ወደ 25ኛው ጉባኤ ተላልፈዋል። በተመሳሳይም ሁኔታ በ25ኛው የአባል ሀገራቱ ጉባኤ ድርድር ውጤቱን ማቅረብ አልቻለም። ምክንያቱም የጋራ የጊዜ ገደቦች አማራጮች ዝርዝር ከሁለት ዓመት (የአምስት ወይም የአሥር ዓመት የትግበራ ጊዜ እ.አ.አ. ለ2025 ወይም ለ2030 የተቀመጡ ግቦች) ወደ 12 ሊሆኑ የሚችሉ ቀመሮች በመቀየራቸው ነው። ይህ ዝርዝር የመጀመሪያውን የአምስት እና የአሥር ዓመት አማራጮችን እንዲሁም ድቅል አማራጭን ያካትታል። የአንዳንድ ሀገራት ተደራዳሪዎች ደግሞ ለታዳጊ እና ለበለፀጉ ሀገራት በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ትግበራ የተለያየ የጋራ የጊዜ ገደቦችን አቅርበዋል። በመሆኑም በ26ኛው የግላስጎ ጉባኤ ተደራዳሪ "ፓርቲዎች" እንደገና በዚህ ንዑስ አጀንዳ ላይ ወደፊት ለመራመድ የሚያስችል ስምምነት ላይ መደረስ ይኖርባቸዋል።

**ወደ ገፅ ፱**

**ከገፅ ፰ የቀጠለ**

**የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ፡** የሚቀጥለው COP 26 ለታዳጊ ሀገራት በጣም አስፈላጊ አጀንዳ በሆነው የማጣጣሚያ ተግባራት ዙሪያም ውጤት እንደሚያመጣ ይጠበቃል። የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም፣ አልበገሬነትን ለማጠናከርና ተጋላጭነትን ለመቀነስ ለሚደረገው ጥረት፤ የፓሪስ ስምምነት አንደኛው አካል በሆነው የአለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ዓለም አቀፍ ግብ ዙሪያ ቀጣይ እርምጃዎችን የሚያራምድ ተጨባጭ የሆነ ውጤት ይጠበቃል።

**የፓሪስ ስምምነት ደንብን ማጠናቀቅ፡** ያለምንም ጥርጥር የፓሪስ ስምምነት ደንብን ማፅደቅ በፓሪስ ስምምነት የተቀመጡትን ድርጊቶች ከመተግበርያ ቅድመ ሁኔታ አንፃር በግላስጎ ከፍተኛ ቅድሚያ ከሚሰጠቸው ተግባራት አንዱ ነው። በተጨማሪም ሳይጠናቀቁ የቆዩ በአየር ንብረትና በሌሎች መንስኤዎች የሚከሰቱ እንደ ኪሳራና ጉዳት፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች እና የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ኮንቬንሽን (UNFCCC) የላቀ ዕቅድ ግብ የCOP26 የውይይት ርዕስ ይሆናሉ ተብሎ ይጠበቃል።

**ኢትዮጵያ ከCOP26 የምትጠብቃቸው እና ቅድሚያ የምትሰጣቸው ጉዳች**

ኢትዮጵያ በUNFCCC ስር በሚካሄደው የአለም አቀፉ የአየር ንብረት ድርድር መድረኮች እ.አ.አ. ከ1992 ጀምሮ ስትካፈል ቆይታለች። ሀገሪቱ በUNFCCC ስር እየተንቀሳቀሱ በሚገኙት ክልላዊና ፖለቲካዊ 3 ቡድኖች ማለትም የአፍሪካ የድርድር ቡድን፣ የታዳጊ ሀገሮችና የG-77ና ቻይና ቡድን አባል ናት።

ኢትዮጵያ የታዳጊ ሀገራትን ፍላጎት በተለያዩ ፎረሞች ላይ ስታንፀባርቅ ቆይታለች። ሀገሪቱ በሚኒስትሮችና በሀገራት መሪዎች መድረክ የአፍሪካ የድርድር ቡድን ቴክኒካዊ አስተሳሰቦች በአግባቡ እንዲፀባረቁ እንዲረዳ በተቋቋመው የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች ኮሚቴና የአየር ንብረት ለውጥ አስተዳደር (CAHOSCC) መስራች አባል ነበረች። በCAHOSCC ስር ኢትዮጵያ በኮፐንሀገን ከተካሄደው COP15 እስከ ደርባን COP17 አፍሪካን በተለያዩ ርዕሶች ወክላለች። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ የታዳጊ ሀገራት ቡድንና የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ፎረምን ከ2008/2009 እስከ 2010 ዓ.ም በሊቀመንበርነት ስትመራ ቆይታለች።

በሀገር ውስጥም የኢትዮጵያ መንግስት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመመከት ቁርጠኝነትን ያሳየ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የላቀ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ አስቀምጥዋል። ኢትዮጵያ ከፓሪስ ስምምነት በፊት በደርባን COP17 በተካሄደው ውጤታማ ድርድር ላይ የረጅም ዘመን ስትራቴጂ የሆነውን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን ነድፎ በማቅረብ ግንባር ቀደም ናት። በፓሪስ ስምምነት መሰረት ኢትዮጵያ እጅግ የላቀ ዒላማ የያዘውን የተሻሻለ NDC ለUNFCCC ያስገባች ሲሆን የ2050 የረጅም ዘመን የዝቅተኛ ካርቦን እድገት ስትራቴጂ ዝግጅትም በሂደት ላይ ይገኛል። በተጨማሪም መንግስት 20 ቢሊዮን የዛፍ ችግኞች ለመትከል ያለመውን የአረንጓዴ አሻራ ትግበራን በ2011 ዓ.ም የጀመረ ሲሆን እስካሁንም 18 ቢሊዮን ችግኝ መትከል ተችሏል።

ኢትዮጵያ እንደ ታዳጊ ሀገራትና የአፍሪካ ተደራዳሪዎች ቡድን ሁሉ በCOP26 ቅድሚያ የምትሰጣቸው ነጥቦች የላቀ ዒላማ ማስቀመጥ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ፣ የካርቦን ንግድ ተሳትፎ ዘዴና የተጠያቂነት ጉዳዮች ናቸው።

የላቀ ዕቅድን በማስቀመጥ ዙሪያ አባል ሀገራት የነበረውን ክፈትት የሚሞላና አዲስ በወጣው 6ኛው የበይነ መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ፓናል ባስቀመጠው ምክረ ሀሳብ መሰረት የ1.5° ሴልሺየስ ግብ የሚያሳካ የተከለሰ NDC በግላስጎ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል። በዚህም መሰረት ያደጉ ሀገራትና ብዙ የልቅት መጠን ያላቸው ሀገራት የትግበራው መሪ መሆን ያለባቸው ሲሆን ልቀታቸውንም መቀነስ አለባቸው። ለዚህም COP26 ዋስትና ሰጥቶ ማለፍ አለበት።. በአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ረገድም ግላስጎ በአለም አቀፉ የማጣጣሚያ ግብ (GGA) ትግበራ ፍኖተካርታ ማስቀመጥ አለበት። በፖለቲካዊና በቴክኒካል ጉዳች ውስብስበነት ምክንያት ሁሉም የGGA ጉዳዮች በግላስጎ ይፈታሉ ተብሎ አይጠበቅም። ፋይናንስን በተመለከተ COP26 እ.አ.አ. ከ2025 በኋላ ትግባራ ሂደትን የማሳክያ አዲስ ግብ ለማስቀመጥ ግልጽ የሂደት አመላካቾች ስምምነት እንዲደረስ ይጠበቅበታል።. በዋነኛነት ያደጉ ሀገራት በግላስጎ በየአመቱ ለአየር ንብረት ለውጥ ትግበራ የሚያስፈልገውን 100 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር መለገስ ስለመቻላቸው ግልጽ ግምገማ ተካሂዶ በቀጣይ እርምጃዎች ላይ ስምምነት መደረስ ይኖርበታል። የፓሪስ ስምምነት አንቀፅ 6ን በተመለከተ በCOP26 ጠንካራ፣ ግልጽ እና በአለም አቀፍ ትክክለኛ የልቀት ቅነሳ ላይ መሰረት ያደረገ የካርቦን ግብይት ደንብ ዝግጅት መጠናቀቅ ይኖርበታል። በመጨረሻም፣ ለተጠያቂነትና ለተሻለ ትግበራ በዋነኛነት የፓሪስ ስምምነትን ከመተግበር አኳያ እንዲሁም ለNDC ትግበራ የጋራ የጊዜ ሰሌዳ በማስቀመጥ ዙሪያ የጋራ መግባቢያ ላይ መደረስ ይኖርበታል።

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን
ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት
ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150
ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com
ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

## ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

## ስራውን የደገፉ አካላት

NDC PARTNERSHIP | IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

Supported by:

MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS OF DENMARK
Federal Ministry for Economic Cooperation and Development
Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety
based on a decision of the German Bundestag
Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands
Norwegian Ministry of Climate and Environment
Norwegian Ministry of Foreign Affairs
Government Offices of Sweden Ministry for Foreign Affairs
UK Government

Climate & Development Knowledge Network
SOUTH SOUTH NORTH TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands
IDRC · CRDI International Development Research Centre Centre de recherches pour le développement international
Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.

.